# የጋራ ተጠቃሚነትን…

**ብሥራት ጥላሁን**

**12-19-14**

የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ህዝቦች ለዘመናት በዘለቀ የእርስ በርስና የድንበር ተሻጋሪ ግጭት ምክንያት ሠላም አጥተው ሲታመሱ የኖሩ ህዝቦች ናቸው። በነበረው የሠላምና የመረጋጋት ችግር ምክንያትም የእርስ በርስ መተማመን ጠፍቶ በጥርጣሬ መልክ ሲተያዩ ኖረዋል። ኢትዮጵያም የነበራት ወታደራዊ መንግሥት በነበረው የደከመ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ምክንያት ከጎረቤቶቿ ጋር ሠላማዊ ግንኙነት አልነበራትም፤ በአገር ውስጥም ቢሆን ምንም ዓይነት ልማት የሚታሰብ አልነበረም።

በዚህ ምክንያት የቀጠናው ሕዝቦች እርስ በርስ በጥላቻ እየተያዩና አንዱ የአንዱን ጉዳት የሚሻ ተደርጎ እየተወሰደ በወቅቱ የነበሩ መሪዎችም የውስጥ ችግሮቻቸውን ለማፈን ሲሉ ይህንኑ እያስተጋቡ ዘመናት አልፈዋል። ሕዝቡም የልማት ተጠቃሚ ሳይሆንና ያለውን ፀጋ በአግባቡ ሳይጠቀምበት በምዕራባዊያን ምጽዋት ላይ ጥገኛ ሆኖ ለመኖር ተገዶ ነበር።

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የሚፈልጉት ግብጽ ሠላምና መረጋጋት የሰፈነባት አገር እንድትሆን ነው። ኢትዮጵያ ከያዘቻቸው ዐበይት  አጀንዳዎች አንዱ በተናጠልም ሆነ በጋራ ልማትን ማረጋገጥ ነው። ይህንን ለማድረግ  የሠላም ፋይዳ የጎላ መሆኑን በመገንዘብ  በአገር ውስጥ፣ በቀጣናውም ሆነ በአህጉር ደረጃ ሠላም ይሰፍን ዘንድ ቀላል የማይባል መስዋዕትነት በመክፈል ላይ ትገኛለች።

በማንኛውም  የአካባቢው አገራት የሚከሰት አለመረጋጋትና የሠላም እጦት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሌሎች አጎራባች አገራት የንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ ጫና ቀላል አይደለም። የቀጠናው ሕዝቦች በዋናነት መታገል ያለብን ድህነትን  በመሆኑ  ግብጻዊያን  ያጋጠማቸውን ችግርም በሠላማዊ መንገድ መፍታት ይችሉ ዘንድ የሁሉም ኢትዮጵያዊ  ምኞት ነው።

የሕዳሴው ግድብ እየተገነባ ያለው በሲርና እና በጉባ መካከል በመሆኑና አካባቢው በተራሮች የተከበበ ስለሆነ ምንም ዓይነት የመስኖ ሥራ ለማከናወን ስለማያመች የውኃ መጠኑ በግድቡ ምክንያት ሊቀነስ እንደማይችል በተደጋጋሚ የተነገረ ቢሆንም “ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ” እንዲሉ ግንባታው ከተጀመረ ከሁለት ዓመታት በኋላ የግብጽ ተቃውሞ በሙርሲና በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በኩል ቀርቧል፡፡

የግብጽና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለዘመናት የዘለቀ ታሪካዊና ባሕላዊ ትስስር አላቸው፤ ፖለቲከኞች በተዛባ መንገድ በተጓዙ ቁጥር ግን ይህ ግንኙነት እንደማይበጠስ አሳይተዋል፡፡ በመሆኑም የተለቀቀው ዛቻ በአብዛኛው ግብጻዊያን በኢትዮጵያውያንና በዓለም ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

በሕዝብ አመጽና በወታደራዊ ኃይል ሥልጣናቸውን እንዲለቁ የተገደዱት መሐመድ ሙርሲ ከአገሪቱ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ተወካዮች ጋር ሆነው የኢትዮጵያን አብዝኃነት ለመከፋፈልና እርስ በርስ ለማጋጨት እንጠቀምበታለን ብለው ነበር፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ የሚገኙትን ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን በመጠቀም የአገሪቱን የልማት ጉዞ ማደናቀፍ ይቻላል የሚል አቋም ላይ ደርሰውም ነበር፡፡ የግብጽ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያዊያን የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ተጠቅመን የአገሪቱን ልማት እናደናቅፋለን ለማለት የደፈሩት ከምን ተነስተው ነው? የሚለውን ማየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

እንደ መድረክና አንድነት የመሳሰሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ በምትገባበት ወቅት የማፈግፈግና ከጠላት ጋር ተባብሮ የተከሰተውን ችግር የማባባስ ተግባርን በተለያየ አጋጣሚ ሲፈፅሙ መስተዋላቸው ምናልባትም የግብጽ ፖለቲከኞች እንደ አንድ መነሻ አድርገው ሊወስዱት ይችሉ ይሆናል፡፡

እድሉ ካጋጠማቸው ኢትዮጵያን ለመምራት እየተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና ከአገር ውጭ ሆነውም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ያገባናል በሚል ሕገ መንግሥቱን ለመናድ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ቡድኖች አገራዊ ስሜት እንደሌላቸው ሌላው መነሻ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

እነዚህ ኢትዮጵያን እናስተዳድራለን በሚል የፖለቲካ ድርጅት መሥርተው እየተንቀሳቀሱ ያሉት ጥቂት የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አልሸባብ ኢትዮጵያን ለመውረር በኢትዮጵያ ላይ የጅሃድ ጦርነት ባወጀበት ወቅትም ክህደታቸውን በይፋ አሳውቀው ነበር፡፡

የሶማሊያው ጽንፈኛ አልሸባብ ሶማሊያን በተቆጣጠረበት ወቅት ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ዒላማው እንደሆነች የጅሃድ ጦርነት ያለውን እንዳወጀባት እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች ኢትዮጵያ የወሰደችው የመከላከል አፀፋን በይፋ ሲያወግዙ ቆይተዋል፡፡

አሁን የግብጽ መንግሥትና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በኢትዮጵያ የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን በመጠቀም የሕዳሴውን ግድብ ለማደናቀፍ እንሰራለን ያሉትም በአገራችን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች የላላ የአገር ፍቅርና ታማኝነት በመመልከት ሊሆን ይችላል፡፡ ተጨባጭ ሁኔታው የሚያሳየውም ይህንኑ ነው።

በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ባላት ግጭትም እነዚህ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኤርትራን ደግፈው ሲሟገቱ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በተለይ የፀረ ሽብርና የመያዶች ሕግ ሲወጣና ሌሎችም ተግባራት ሲሰሩ ቀድመው በመቃወምና ከጠላት ሥር በመሰለፍ የሚታወቁት መድረክና አንድነት ዛሬም ለግብጽ በጎ ምላሽ ይሰጣሉ ተብሎ በመገመቱ ነው፡፡

የግብጽ ፖለቲከኞች ግምት ሙሉ በሙሉ ስህተት ነው ማለት አይቻልም፡፡ የግብጽ አቋም ይፋ በሆነ ማግሥትም አንድነትና መድረክ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ተቃውሞ አሰምተዋል፡፡ "የሕዳሴው ግድብ የማን እንደሆነ አይታወቅም ሲሉም አሳፋሪ መግለጫ አውጥተዋል፡፡

በአገሪቱ ብሔራዊ መግባባት የለም፣ የሕዳሴው ግድብ ሕዝቡ ሳያውቀው በድብቅ ሲካሄድ ቆይቷል፣ ሕዝቡ ከፍላጎቱ ውጪ በግድ ቦንድ እንዲገዛ እየተደረገ ነው፣ ግድቡ ይቁም" የሚሉ አሳፋሪ ነጥቦችን በመግለጫቸው አስፍረዋል፡፡

አገሪቱ ወሣኝ ሁኔታ ሲያጋጥማት እየተሸበለሉ ከጠላቶቻችን ጎራ የሚሰለፉት እነዚህ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በእውነቱ ለሕዝብ እንዳልቆሙ በራሳቸው መንገድ እርቃናቸውን ወጥተዋል፡፡ የሕዳሴው ግድብ የማን ሊሆን ኖሯል? ይህ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም፡፡ በደርግም ሆነ በአጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ የተገነቡ የልማት ሥራዎች ደርግ ወይም ኃይለሥላሴ ይዘዋቸው አልሄዱም፡፡

የፖለቲካ ድርጅት ይቀያየራል፡፡ በአንዲት ዴሞክራሲያዊት አገር የሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን በተረጋገጠበት አገር መንግሥት መቀያየሩ የግድ ነው፡፡ ኢህአዴግም ሕዝቡ እስከመረጠው ብቻ ነው ሥልጣን ላይ የሚቆየው፡፡ አሁን እየተገነቡ ያሉ ትላልቅ ልማቶች የሕዝብ ቅርሶች መሆናቸው ጥያቄ የሚገባ አይደለም፡፡

በሕዳሴው ግድብ ከእነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች በስተቀር መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አባይን ያህል የተፈጥሮ ፀጋ ይዞ መራቡና መሰደዱ ለዓመታት ሲቆጨው የነበረ በመሆኑ አሁን እንደዚህ ዓይነት ልማት በአባይ ላይ ሲዘረጋ ያለምንም ልዩነት ልማቱን ዳር ለማድረስ በአንድ ድምጽ መነሳቱ የሚታወቅ ነው፡፡ በሕዳሴው ግድብ ብሔራዊ መግባባት እንዳለ የሚያጠያይቅ ነገር የለም፡፡

ይሁንና ግብጻዊያኑ በአገር ውስጥ መግባባት ስለሌለ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንጠቀማለን ሲሉ መድረክም በኢትዮጵያ  መግባባት የለም ግድቡም መቆም አለበት የሚል መግለጫ በአገር ውስጥ ተቀምጦ ሲያስተጋባ ተደምጧል፡፡ እንግዲህ መድረክና አንድነት አሁንም ለግብጽ መሣሪያ ለመሆን ዝግጁ ላለመሆናቸው የሚያስተማምን ነገር የለም፡፡

ይህ አይሆንም ማለት አይቻልም፡፡ ካሁን ቀደም ከነበረው የመድረክና የአንድነት አቋም በመነሳትም መገመት ይቻላል፡፡ እነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች የተቋቋሙትና በመንቀሳቀስ ላይ ያሉት በአገሪቱ የተፈጠረውን የአብዝኃ ፓርቲ ሥርዓት በመጠቀም ነው፡፡

የአገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነው ሕገ መንግሥት በሰጣቸው መብት መሠረት ነው፡፡ መብቱን እየተጠቀሙ ሥርዓቱን ከሕገ መንግሥት ተጻራሪ በሆነ መንገድ ለመሸርሸር መንቀሳቀሳቸው እጅግ ያስገርማል፤ ማንነታቸውን ያሳያል።

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የግብጽ የፖለቲካ ድርጅቶች የሕዳሴውን ግድብ ለማደናቀፍ ልብ ለልብ የተናገኙ ቢመስሉም ግድቡ የሕዝቡ በመሆኑ ማለፊያ መንገዱ ዝግ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ለአንድነታቸው፣ ለነፃነታቸውና ለክብራቸው ለአፍታ የማያመነቱ መሆናቸው እሙን ነው፡፡

በመሆኑም በልማታቸው የሚመጣባቸውን ማንኛውም ወገን መሸከም አይችሉም፡፡ መድረክና አንድነትም የኢትዮጵያን የሕዳሴ ግድብ ለማስቆም ላይ ታች እያሉ ከሚገኙ የኤርትራ መንግሥትና የግብጽ ጥቂት ፖለቲከኞች ለይተን አናያቸውም፡፡

በግብጽ ያለው ሁኔታ መሐመድ ሙርሲና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ተጠሪዎች እንዳቀረቡት አይደለም፡፡ በዚህ ሃሳብ የሚስማሙ ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ የግብጽ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ግንኙነት በሠላማዊ መንገድ ማራመድ ሁለቱንም ሕዝቦች ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ለዚያም ነው በርካታ የግብጽ ምሁራን ሙርሲ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ሳይቀር ማንኛውንም አማራጭ እንጠቀማለን ማለታቸውን የተቃወሙት።

የኢትዮጵያ ሕዝብም ቢሆን የግብጽን ሕዝብ የሚጎዳ ነገር ማድረግን አይፈልግም፡፡ አባይ ግብጽም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ የልማት ፍላጎት ለመመለስ የሚያስችል አቅም ያለው የተፈጥሮ ፀጋ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በወንዙ  የአቅሟን ያህል ብታለማ ግብጽ አሁን እየተጠቀመች ያለውን የውኃ መጠን ይቀንሰዋል ተብሎ አይገመትም፡፡

በተለይ ደግሞ የሕዳሴው ግድብ የግብጽን የውኃ መጠን እንዲጨምር ያግዛል እንጂ እንዲቀንስ የሚያደርግበት ሁኔታ የለም፡፡ ግድቡ የሚሰራው በትልቅ ሸለቆ ውስጥ በመሆኑና አካባቢው በተራራ በመከበቡ ኢትዮጵያ ከግድቡ የሚገኘውን ውኃ ለኤሌክትሪክ ማመንጫ ብቻ ስለምትጠቀምበት ውኃው የሚቀንስበት ምክንያት የለም፡፡

ውኃው ኤሌክትሪኩን እያመነጨ ወደ ሱዳንና ግብጽ ጉዞውን ይቀጥላል፡፡ ሱዳንም ሆነች ግብጽ ከዓመት ዓመት መጠኑን ያልቀነሰ ውኃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

የሱዳን መንግሥት ይህንን በመረዳት ከኢትዮጵያ ጋር ተባብሮ ለመሥራት ፍላጎቱን እየገለፀ ይገኛል፡፡ በተጨባጭም ሁለቱ ሱዳኖች የሕዳሴው ግድብ በሚመለከት ከግብጽ የተነሳውን ሃሳብ አውግዘዋል፡፡ ሌሎች የላይኛው ተፋሰስ አገራትም በተመሳሳይ መልኩ ሃሳባቸውንና  አቋማቸውን አሳውቀዋል፡፡

ሱዳን ከዚህ ግድብ በርካታ ጥቅሞችን ታገኛለች፡፡ አንደኛው ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይልን በተመጣጣኝ ዋጋ ገዝታ መጠቀም ትችላለች፡፡ ሌላው ደግሞ በየዓመቱ ደለል ለማስወገድ ታወጣ የነበረውን  ገንዘብ ለሌላ ልማት ታውላለች፡፡

ግብጽም በተመሳሳይ መልኩ ተጠቃሚ ትሆናለች፡፡ ኢትዮጵያና ግብጽ የሁለቱን አገራት ሕዝቦች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚችሉት በጋራና በእኩልነት መርህ ላይ ተመስርተው በትብብር አባይን መጠቀም ከቻሉ ብቻ ነው፡፡ ግብጽ ከኢትዮጵያ ጋር ተግባብታ መሥራት እስካልቻለች ድረስ ውሎ አድሮ ጉዳቱ ለግብጽ ነው።

የአባይ ውኃ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ በገፀ ምድሯ ያለውን የተፈጥሮ ፀጋ ለመጠቀም የሚከለክላት አህጉራዊም ሆነ አለም አቀፋዊ ሕግ የለም፡፡ በአገሪቱ ያለው መንግሥትም ልማታዊ በመሆኑ የጀመረውን ልማት ዳር ለማድረስ ያላሰለሰ ጥረት ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም፡፡

የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሣለኝ በቅርቡ ለሚዲያ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት ኢትዮጵያ በሕዳሴው ግድብ ግንባታና በሚያመነጨው የኃይል መጠን ዙሪያ ከግብጽ ጋር የማታደርገው ምንም ዓይነት ድርድር አይኖርም፡፡ የግንባታውን ፍጥነትም አይቀንስም ብለዋል፡፡ ይህ ቀደም ሲል የነበረ አቋም አሁን በቀጣይነት የሚኖር የፀና አቋም እንደሆነም አስምረውበታል፡፡

ለግብጽ ሕዝብና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበጀው በጋራ መልማትን ነው፡፡ በጋራ ለመልማት ደግሞ ግብጽ እያራመደች ያለውን የ1959 የቅኝ ግዛት ወቅት ስምምነት

ጊዜው ያለፈበትና ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችበት በመሆኑ እሱን ወደ ጎን በመተው በአዲሱ የትብብር ስምምነት መፈረምና ከአባይ ተፋሰስ አገራት ጋር ተባብራ መሥራት ስትችል ነው፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቢሆኑ የሕዝብ ፍላጎት ማንበብና ለሕዝብ መሥራት ሲኖርባቸው አገራችንን የሚፈታተን ነገር በተከሰተ ቁጥር በገንዘብ እየተሸጡ መቀጠል አይችሉም፡፡

ግንቦት 7 በመባል የሚታወቀው ቡድን ከኢሣያስ አፈወርቂ የአምስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ ማግኘቱን ይፋ አድርጓል፡፡ ይህ አንድ ማሣያ ነው። ሌሎችም በግላጭ ስለማይነገር ካልሆነ በስተቀር ከዚህ የራቁ ለመሆናቸው መተማመኛ የለም። ከዚህ ድርጊታቸው ሊታቀቡና በጋራ አልምቶ በጋራ መጠቀም ለሁለቱ ሕዝቦች የሚጠቅም መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል።

የአባይ ተፋሰስ 3 ነጥብ 37 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ቦታን ይሸፍናል። ይህ የአፍሪካ አህጉርን 10 በመቶ የሚሆነውን መሬት ማለት ነው። የአባይ ወንዝ  በተፋሰሱ ዙሪያ ያሉትን አገራት ሁሉ ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል በቂ አቅም አለው። የሁሉንም የአባይ ተፋሰስ አገራት የልማትና የእድገት ጥያቄ  መመለስ የሚችል የተፈጥሮ ፀጋ ነው።

ለዚህ ግን በቀጠናው ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋትን የግድ ይላል። በተፋሰሱ ዙሪያ ያሉ አገራት ለጋራ ጥቅም የልማት ትብብራቸውን ማጎልበት ይጠይቃል። የአባይ ተፋሰስ መንግሥታት በሚያደርጉት ሠላማዊና ልማታዊ ትብብር ቀጠናው በኢኮኖሚ ተሳስሮ ያድጋል በተፋሰሱ የሚኖሩት 160 ሚሊዮን ሕዝብም ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀምንና አስተዳደርን በአስተማማኝ መንገድ መዘርጋት የተፋሰሱን የላይኛውም ሆነ የታችኛው አገራት ሕዝቦችን ተጠቃሚ ከማድረጉ ጎን ለጎን  በቀጠናው ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን ያስችላል። ሠላም በአስተማማኝ መልክ ሰፈነ ማለት ደግሞ

የኢኮኖሚ ትስስሩ እየጠነከረ ስለሚሄድ ሁሉም ወገን በየደረጃው ተጠቃሚ ሆኗል። ከእድገቱ የላይኛውም ሆኑ የታችኛው የተፋሰሱ አገራት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ለዚህም ነው በአባይ ተፋሰስ ላይ የሚገነባ ማንኛውም ዓይነት ልማት ማንኛውንም አገር የሚጎዳ አይሆንም የሚባለው። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እየተገነባ ያለው ታላቁ የሕዳሴው ግድብም ጠቀሜታው ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሱዳንና ለግብጽም ጭምር መሆኑ እሙን ነው።

ከዚህ በመነሳትም ግብጽ  አባይ ላይ የሚከናወኑ ልማቶች ይጎዱኛል በማለት ለዓመታት ስታራምደው የቆየችውና አሁን በቅርብ ጊዜ ብቅ ያደረገችው እምነትም ውኃ አለመቋጠሩን ለመገንዘብ አያዳግትም። ሥጋቱ ከተጨባጭ መነሻ በጥናት ተደግፎ የሚነሳ ሳይሆን ቀደም ሲል ከነበረው ሽኩርታ የመነጨ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በቅርቡ ከታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ጋር ተያይዞ የአባይ ወንዝን በጊዜያዊነት ከተፈጥሯዊ መፍሰሻ መስመሩ መቀልበሱን ተከትሎ ከግብጽ የተሰማው ጊዜ ያለፈበት አስተሳሰብ ለማምንታት አጀንዳ ሆኖ ቆይቷል፡፡

የቀድሞው የግብጽ ፕሬዚዳንት መሐመድ ሙርሲ በአገሪቱ ከሚገኙ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ተወካዮች ጋር ባደረጉት ውይይት እንዳስታወቁት የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ለማደናቀፍ ማንኛውንም ዓይነት አማራጭ ለመጠቀም ወደ ኋላ እንደማይሉ ለማወቅ ተችሏል። ይህ ቀረርቶ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የዓለምን ኅብረተሰብ ያስደመመ ሁኔታ ነበር፡፡

ፕሬዚዳንቱ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ጋር ባደረጉት ውይይት እንደተደመጠው በኢትዮጵያ የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን በእጅ አዙር መጠቀም፣ የኢትዮጵያ ጎረቤት አገራትን በመደገፍና በማስታጠቅ ከኢትዮጵያ ጋር በሠላማዊ መልክ እንዳይኖሩ ማበጣበጥ፣ በኢትዮጵያ በሚገኘው የግብጽ ኤምባሲ አማካይነት የስለላ ቡድን በማደራጀት  የአገሪቱን ትላልቅ የልማት ተቋማትን በመለየትና በምን መልክ ማስተጓጎል እንደሚቻል በማጥናት ጥፋት መፈፀም የሚችል ቡድን እያደራጁ ሥምሪት ማድረግ የሚሉ ይገኙበታል። እነዚህ አማራጮች ካልሰሩ ደግሞ የጦርነት

አማራጭን የመጠቀምና ግድቡን መደብደብ የሚሉ ሃሳቦችን አቅርበው በይፋ ተወያይተዋል፡፡

ኢትዮጵያን የማተራመስ ዓላማ በነበረው ውይይታቸው በማንኛውም መልክ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ማደናቀፍ የሚያስችላቸውን አማራጭ ሁሉ መጠቀም እንደሚፈልጉ ተናግረዋል።

ሆኖም ግን ከጊዜ በኋላ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በማየት ሰከን ብለው ሲያስቡት የነደፏቸው ሥልቶች በሙሉ የኢትዮጵያን ልማት ለማደናቀፍ የሚችሉ እንዳልሆኑ በመገንዘብ ወደ ድርድር መምጣትን መርጠዋል። ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ እያደገችና እየፈረጠመች የመጣች አገር፣ ሕዝቦቿም ልዩነት ውበታቸው መሆኑን በመገንዘብ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነታቸውን ያረጋገጡበት ወቅት በመሆኑ ነው፡፡

እንዲሁም አገሪቱ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ደረጃ ያላት ተሰሚነት እየጨመረ ስለመጣና ከጎረቤት አገራት ጋር ያላት የሁለትዮሽ ግንኙነት መልካም በመሆኑ እነዚህ የማተራመስ ስልቶች እንደማያዋጡ የተገነዘቡ አንዳንድ ምሁራኖቻቸው ኢትዮጵያን ይቅርታ እንዲጠይቁ እየገፋፏቸው ይገኛሉ።

ግብጻዊያኑ ይህንን ሁሉ ሲያቅራሩና ሲለፍፉ ኢትዮጵያ ጉዳዩን በትዕግሥት ትከታተለው ነበር። አገሪቱ የጦርነት አማራጭን የምትወስደው ለመከላከል ብቻ እንጂ ለእብሪትና ለወረራ እንደማትጠቀምበት በሕገ መንግሥቷ በግልጽ አስፍራለች። ይሁንና ግብጻዊያን ወንድሞች እያነሱት ያለው ነገር አግባብ ባለመሆኑ በጥሞና ሊያዩትና ሊመረምሩት እንደሚገባ በማሳወቅ ጭምር።

አንድም የኢትዮጵያን ጥንካሬ በማየት በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገራት ጋር ያላትን መልካም ግንኙነት ለማግባባት ከሄዱባቸው አገራት በመረዳትና ከዚያም አልፎ ኢትዮጵያ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ ያላትን ተቀባይነት በመገንዘብና ዓለም አቀፍ ሕግጋትን በማየት ከድርድር ውጭ ምንም ዓይነት አማራጭ እንደማይኖር በመረዳት ወደ ድርድር መጥታለች።

ኢትዮጵያ በግብጽ በኩል የተፈጠረውን ጠብ አጫሪነት በትዕግሥት በማለፍ በግብጽ እየተነሳ ያለው ሥጋት ትክክል እንደዳልሆነ የግብጽ ህዝብ እንዲያውቀው ለማድረግ የተቻለውን ያህል ጥረት አድርጋለች።

ከታላቁ የህዳሴው ግድብ ጋር ተያይዞ እየተነሳ ያለው ጥያቄ በሠላማዊ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ ባደረገችው ጥረትም  የግብጽ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከኢትዮያ አቻቸው ጋር መወያየትን መርጠዋል።

ሁለቱ አካላት ባደረጉት ውይይት ከቀረርቶና ከእብሪተኝነት ይልቅ በጋራ ጥቅም ላይ ያነጣጠረ የሁለትዮሽ ውይይት ማድረግ ጠቃሚ መሆኑን በመረዳዳት በቀጣይ ውይይቱን ለማጠናከር ለጉዳዩ ሠላማዊ መፍትሄ ለመፈለግ የሚያስችል የመነሻ ነጥብ አስቀምጠዋል፡፡

በተለይም ደግሞ ታላቁ የኢትዮጵያ መሪ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በሕይወት ዘመናቸው ታላቁን የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ባስጀመሩበት ወቅት ግብጽ መንግሥት ስላልነበራት የግብጽ ሕዝብ እርስ በርሳችን በተበጠበጥንበትና የመደራደርና የመከላከል አቅም ባልነበረን ወቅት ኢትዮጵያ አባይ ወንዝ ላይ ትልቅ ግድብ ገነባች የሚል ግንዛቤ  እንዳያሳድር ጥረት ተደርጓል፡፡

ፀረ ልማት ቡድኖቹ ከግድቡ ጋር በተያያዘ ሊያናፍሷቸው በሚችሉ አሉቧልታዎች እንዳይወናበድ ለመርዳት በማሰብ ከግብጽ፣ ከሱዳንና ከኢትዮጵያ የተውጣጡ ባለሙያዎች ከዓለም አቀፍ የዘርፉ ኤክስፐርቶች ጋር በመሆን የህዳሴው ግድብ ለታችኛው አገራት ማለትም ለግብጽና ለሱዳን ምንም ዓይነት ጉዳት እንደማያመጣ አጥንቶ አቅርቧል፡፡

የግብጽ፣ የሱዳንና የኢትዮጵያ ሕዝብም የኢትዮጵያ መንግሥት በጥናት ካረጋገጠው በተጨማሪ ዓለም አቀፍ ጥናቱን በማወቅ በተረጋጋ መልክ ልማቱ እንዲካሄድ ለማስቻል ነበር፡፡በወቅቱ የግብጽ የሕዝብ ዲፕሎማሲ ወኪሎችም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር ባደረጉት ውይይት እውነታውን ተገንዝበው መሄዳቸው ይታወሣል፡፡ ይህ ጉዳይ ከተከናወነ ሦስትት ዓመት አለፈው፡፡

ዓለም አቀፍ የኤክስፐርቶች ቡድንም በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ጥናትና ምርምር በማድረግ ከ700 ገጽ በላይ ሪፖርቱን አጠናቅሮ ለየአገራቱ አቀረበ፡፡ ሪፖርቱ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ በተፋሰሱ አገራት የሚያደርሰው ጉዳት እንደሌለም አስታወቀ፡፡

በዚህ መካከል ግንባታው በመፋጠን ያለው ታላቁ የሕዳሴ ግድብ አንድ ምዕራፍ ላይ በመድረሱ የአባይ ወንዝ በጊዜያዊነት ከተፈጥሯዊ ፍሰቱ መቀልበስና በሌላ መንገድ እስከ ተወሰነ ርቀት ሄደ መልሶ ወደ መስመሩ እንዲገባ የማድረግ ተግባር በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ተከናወነ፡፡

ይህ ተግባር በኢትዮጵያዊያን ይሰራል ተብሎ አይገመትም ነበር፡፡ አባይን ያህል ወንዝ ማስቀየስ ለኢትዮጵያውያን ኩራት ቢሆንም በግብጽ በኩል ግን እንደ አዲስ ነገሩ አገርሽቶ አስፈላጊ ያልሆነ ማለትም ኢትዮጵያን የማተራመስ እቅድ ተነደፈ፡፡

ከመጀመሪያው ጀምሮ በግብጽ ይነሳ የነበረው ሥጋት ኢትዮጵያ በአባይ ላይ መገንባት የሚቻለውን ትልቁን ግድብ ከሰራች ለግብጽ የሚመጣው የውኃ መጠን ስለሚቀንስ ሕዝቤ ተጎጂ ይሆናል የሚል ነበር፡፡ ይህ እሳቤ በወቅቱም ተነስቶ በተለያዩ ሚዲያዎች ሲራገብ እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ የግብጽን ሕዝብ የሚጎዳ ምንም ዓይነት ሥራ እንደማይሰራ በተደጋጋሚ ጊዜ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ለግብጽም ሆነ ለሱዳን የጎላ ጠቀሜታ ስለሚኖረው በጋራ ሰርተን በጋራ እንጠቀም የሚል መልዕክትም ሲተላለፍ ቆይቷል፡፡

ይህን ሚዛናዊ ትንተና ከሰሙት የግብጽ ምሁራን መካከል ጉዳዩ ትክክል መሆኑን ያመኑ በርካቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖች ይህንን እምነታቸውን አሁንም ድረስ በተለያዩ ሚዲያዎች እየገለጹ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ መንግሥትም ቀደም ሲል የነበረው ቃል እንደተጠበቀ መሆኑን በአጽንኦት በማስረዳት ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ልማት ግብጽን በብዙ መልኩ ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም በሚል።

ታላቁ የሕዳሴው ግድብ በሚገነባበት አካባቢ የሚለማ እርሻ የለም፡፡ በዚህ ግድብ የሚጠራቀመው ውኃም የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨት በስተቀር ለመስኖ አያገለግልም፡፡ በመሆኑም ተርባይኖቹን እያሽከረከረ ወደ ሱዳንና ግብጽ መፍሰሱን ይቀጥላል። በዚህ ምክንያት የሚባክን ውኃ አይኖርም፤ ሱዳንና ግብጽ ያገኙት የነበረው የውኃ መጠንም አይቀንስም፡፡

ግብጽና ሱዳን ከዚህ ግድብ የሚያገኙት ጠቀሜታ የጎላ መሆኑን ግን ግብጻዊያን ወንድሞች ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ እስካሁን ድረስ ባለው መረጃ መሠረት ሱዳን ወንዙ በሚሞላበት ጊዜ ለጎርፍ አደጋ ትዳረግ ነበር፡፡

ይህንን ለመከላከልና በአገሪቱ የሚከማቸውን ደለል ለማስወገድ ለውኃ ከምትይዘው ዓመታዊ በጀት 70 በመቶ የሚሆነውን ለዚሁ ተግባር ታውለው እንደነበር ይታወቃል፡፡ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ከተገነባ በኋላ ግን አገሪቱ ከችግሩ ትላቀቃለች። ሰባ በመቶ የሚሆነው የውኃ በጀቷን ለሌላ ልማት ማዋል ያስችላታል። ግብጽም ከተመሳሳይ ችግር እንድትላቀቅ እንደሚያስችል መረጃዎች ያሳያሉ።

የአባይ ውኃ ከዓመት ዓመት እኩል መጠን የለውም፤ በክረምት ይሞላል በበጋ ይጎድላል፡፡ ከዚህ የተነሳ አገራቱ በቂ መጠን ያለው ውኃ የሚያገኙት በዓመት አራት ወራት ብቻ ነው፡፡ በቀሪዎቹ ወራት የውኃው መጠን ስለሚቀንስ ሱዳንና ግብጽ የሚያገኙት የውኃ መጠንም ይቀንሳል፡፡ ከታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ በኋላ ግን አገራቱ እኩል መጠን ያለው ውኃ ከዓመት ዓመት ማግኘት ይችላሉ።

የወንዞች ውኃ መጠን ቢቀንስም ወደ አገራቱ የሚፈሰው ውኃ በግድቡ ምክንያት መጠኑን አይቀንስም። ሌላው ደግሞ ግድቡ የሚሰራው በጥልቅ ጎርጅ ውስጥ በመሆኑ የውኃ ትነትን ይቀንሳል፡፡ የትነት መጠኑ በቀነሰ ቁጥር አገራቱ የሚያገኙት የውኃ መጠን ይጨምራል፡፡ በዚህ ደግሞ አገራቱ የመስኖ ሥራቸውን አጠናክረው ለመከወን ያግዛቸዋል፡፡

በጥቅሉ ሲታይ በኢትዮጵያ እየተገነባ ያለው የህዳሴው ግድብ በግብጽና በሱዳን ላይ የሚያስከትለው ጉዳት አለመኖሩን መገንዘብ ይቻላል። ይልቁንም ከላይ የተዘረዘሩትን

ጠቀሜታዎችን ከማስገኘቱም በላይ አገራቱ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው ይችላል።

ሱዳን ከኢትዮጵያ አዋሣኝ ለሆኑ ግዛቶቿ የኤሌክትሪክ ኃይል ከኢትዮጵያ ገዝታ ለመጠቀም ትችላለች። ግብጽም በተመሳሳይ መልኩ መጠቀምን የሚያግዳት ነገር የለም። በመሆኑም ግድቡን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ከአፍራሽ እንቅስቃሴ በመራቅ ሦስቱም አገራት ለጋራ ፍትሃዊ እድገት በጋራ ሊንቀሳቀሱ ይገባል።